የሰው ልጅ በባህሪው በአካልም ይሁን በመንፈስ ብቻውን ሲሆን ብዙ ስሜቶችን ለማድመጥ ሰፊ እድል አለው።እነዚህ እንደ ፍርሃት፣ድንጋጤና ስጋት አይነት ስሜቶች ደግሞ ሰው ከአደጋ እንዲጠነቀቅ ፤ ራሱንም እንዲያጠይቅ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው ብዬ አምናለሁ።

ይህን ያልኩት ያለምክንያት አይደለም።ይልቁንስ የአሸናፊዎች አሸናፊ የሆነው፤ በአይን የማይታየው፤ በእጅ የማይዳሰሰው፤ ቢተኩሱበት የማይሞተው፤ ቢያነፈንፉት የማይሸተው፤ በዋጋ የማይገመተው፤ ቢነቁት የማይነቅ ቢተውት የማይተው፤ የልዕለ ሃያላኑ ሀገር አለቃ "የማይታይ ቫይረስ" መሆኑን ስናውቅ ብዙ እንድናስብ ያደርገናል።

ይህን የአሸናፊዎች አሸናፊ ደግሞ ማሸነፍ የምንችለው ራሳችንን ስናሸንፍ ብቻ መሆኑን ስንረዳ ታላቁ ክብራችን ያለው እኛ ላይ መሆኑ ይገባናል።የሃያልነት ትልቁ ሃያልነት ህንፃ ሳይሆን፤ የሃያልነት ትልቁ ሃያልነት ገንዘብ ሳይሆን ራሳችን እኛ መሆኑ ትዝ ይለናል።

ትልቁ አቅም ያለው የሚታየው ጋር ሳይሆን የማይታየው፤ የምንናፍቀው ሳይሆን እኛ ራሳችን ከሆነው ውስጥ አንዱ ነውና ራሳችንን ባግባቡ ልናየው እድላችን አሁን ነው። ጨለምተኛው በፊቱ ባገኘው እድል ሁሉ ውስጥ ያለውን አስቸጋሪ ነገር ያያል፤አዎንታዊዉ ግን በገጠመው ችግር ሁሉ ውስጥ ያለውን ዕድል ይመለከታልና የታሰረው እግራችን እንጂ ጭንቅላታችን ስላልሆነ ፤ለዚህም የተለያዩ ገደቦች በፊታችን ሊቀመጡ ቢችሉም ከማሰብ ፣ከመጠየቅ እና ከማወቅ ግን ሊከለክሉን ስለማይችሉ ይህን ቤት የመዋል መልካም አጋጣሚን ባግባቡ ልናጣጥመው ይገባል።

እውቀታችንን ከኑረታችን፤ የተረዳነውን ከሁነታችን፤ የምናውቀውን ከራሳችን፤ ያለንን ከፍላጎታችን፤ የናፈቅነውን ከስሜታችን አንፃር ልናየው ግድ ይለናል።ያለዚያ ማወቅ ብቻውን በቂ አይደለም፤በተግባር ላይ መዋል አለበትና...

ብዙዎቻችን አዕምሯችንን የሞላው መረጃ ብቻ መሆኑ ዋጋ ሳያስከፍለን እንዳልቀረ አምናለሁ። ለዚህም የአንዳንድ ሰዎች የእውቀት ብዛት መረጃን ከማቀበል ወይም የአጠቃላይ እውቀት ውድድርን ከማሸነፍ ውጭ ጥቅም ሳይሆን እያየነው አለመታዘባችን በራሱ ችግሩን እጥፍ ያደርገዋልና፤ ለዚህም ማስተዋላችን ሙሉ እንዲሆን የሆነብንን ሁሉ አስበን፣ምናልባት በሚሆንብንም ሳንደናገጥ ፣መረጃን ከራስ እውነታ ጋር በማናገድ ውስጣዊ ጥናትን (ተመስጦ) እናደርግ ዘንድ ምክራዊ ትዝብቴ ነው።

ሚያዝያ 13 /2012

እንግዳሸት!¡!¡